## ዜናዎች።

### ዕንቍጣጣሽ፥ ርእሰ ዐውደ ዓመት።

መስከረም ፩ ቀን ፳፻፪ ዓ• ም•

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን! እግዚአብሔር አምላካችን እንኳን ለ፳፻፪ ዓመተ ምሕረት የዘመን መለወጫ በዓል አደረሳችሁ። እንደሚታወቀው አባታችን አለቃ አያሌው ታምሩ በሕይወት በነበሩ ጊዜ በዓላትን ምክንያት በማድረግ ለምእመናን ይጠቅማል ያሏቸውን መልእክቶች ያስተላልፉ ነበር። እኛም ይህንን በማስታወስ እንዲሁም ለዕረፍታቸው ሁለተኛ ዓመት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ይህን በተለያዩ ጊዜአት ካስተማሯቸው ትምህርቶች የተጠናከረ ጽሑፍ አቅርበናል።

እግዚአብሔር አምላካችን በዓሉን የተባረከ ያድርግልን። መጪውንም ዘመነ ማርቆስ የሰላም፥ የጤና፥ የፍቅር፥ የሃይማኖት እንዲያደርግልን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን፤ አሜን። [ተጨማሪ።](#)

### የታላቁ መንፈሳዊ አባትና ሊቅ የአለቃ አያሌው ታምሩ ዕረፍት ፪ኛ ዓመት መታሰቢያ በደማቅ መንፈሳዊ ሥነሥርዐት ተከበረ።

ነሐሴ ፲፬ ቀን ፳፻፩ ዓ• ም•

የክቡር አባታችን የአለቃ አያሌው ታምሩ ዕረፍት ፪ኛ ዓመት መታሰቢያ በዓል ነሐሴ ፲፬ ቀን ፳፻፩ ዓ ም በደማቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐት ተከብሮ ዋለ።

በዕለቱ ከጠዋቱ ፯ ሰዓት ላይ በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የክቡርነታቸው መቃብር በሚገኝበት ስፍራ ላይ ካህናተ እግዚአብሔር፥ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፥ ቤተሰብ፥ ወዳጅና ዘመድ እንዲሁም ተማሪዎቻቸው በተገኙበት የጸሎት ሥነ ሥርዐት ተካሂዷል።

በመቀጠልም ታላቁ አባት ለ፴፯ ዓመታት በኖሩበት፥ በጸለዩበት፥ በግዞት በኖሩበትና ጉባኤ ወንጌል ባካሄዱበት መኖሪያ ቤታቸው በመሄድ ጸሎተ ፍትሐት ተከናውኗል።በዚሁ ጊዜ የክቡር አባታችንን ሕይወት የሚያዘክሩ ቅኔዎችና ዝማሬዎች ቀርበዋል። የቅኔዎቹና የዝማሬዎቹ ምስጢርና ውበት የሥነ ሥርዐቱን ታዳሚዎች ልብ የነካ ነበር። [ተጨማሪ።](#)

### ጾመ ፍልሰታ።

ነሐሴ ፩ ቀን ፳፻፩ ዓ• ም•

እንኳን ለጾመ ፍልሰታ በሰላም አደረሰዎ። ጾመ ፍልሰታ እንደሚታወቀው በአገራችን ዐዋቂዎች ብቻ ሳይሆኑ

ሕፃናት ሳይቀሩ የሚጾሙት ጾም ነው። ጾሙም ብዙ ጸጋና በረከት የሚያሰጥ ነው። ተጨማሪ።

## <u>በዓለ ትንሣኤ።</u>

ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፪ሺ፩ ዓ• ም•

**«ተንሥአ በከመ ይቤ።»** «እነሣለሁ እንዳለ ተነሣ።» (ማቴ፤ ም ፳፰፥ ቊ ፮።)

ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ በመተላለፉ ምክንያት በሕይወቱ ሞት ተፈረደበት። «አንተ መሬት ነህ፤ ወደ መሬት ትመለሳለህ፤» ተባለ።

ማንኛውም ወንጀለኛ በሠራው ጥፋት ሲፈረድበት ሁለት ዐይነት መቀጫ አለ። ከእነዚህም አንዱ ሕግን በመተላለፉ የሚከፍለው መቀጫ ሲሆን፤ ሁለተኛው ለተበዳዩ የሚከፍለው ካሣ ነው። አዳም ሕግን በመተላለፉ በሥጋው ወደ መቃብር፥ በነፍሱ ወደ ሲኦል መውረድ ተፈርዶበት በሞተ ሥጋ፥ በሞተ ነፍስ ተቀጣ። ካሣ ግን የሚከፍለው አልነበረውምና እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ካሠለት። ስለዚህም ከሕይወት ወደ ሞት እንደ ሄደ ከሞት ወደ ሕይወት መመለስ ያስፈልገው ነበር። ስለዚህ ሰው የሆነው አምላክ በሞቱ ሞትን አጠፋለት። በመቃብሩም ሙስና መቃብርን አስቀረለት። በትንሣኤውም ትንሣኤን መሠረተለት። ይህን የቤዛነት ሥራ ለመፈጸም ክርስቶስ የሄደበትን የመስቀል ጉዞ ስንመረምር ከመሥዋዕትነቱ ማለት ከስቅለቱ፥ ከሞቱ ተነሥተን ትንሣኤውን ዕርገቱን እናያለን። ለሰውም የሰጠውን አዲስ ሕይወት እንመ